# ኢትዮጵያ የእምቧይ ካብ አይደለችም።
# ጠላቶቿ ሊያፈርሱት በማይችሉት የሕልውና ስልትና ምስጢር ለዘመናት የተደራችና የተገነባች፣ዘላቂና ሕያው ስለሆነች አትፈርስም- አትበታተንም ስለዚህ ወገን ሁሉ አትስጋ !

ከአስተዋይ በቀለ

በጥልቅ አለማሰብ፣ በማንኛውም ነገር አለመጠንቀቅና ሁሉን አውቃለሁ ብሎ እንደ እሾህ ማገዶ መንጣጣት የዳያስፖራው መለዮና የስህተት መንገድ ሆኖ ይታያል። ከዚህ ተጠቃሚዎቹ እንደ ግንቦት 7 የመሳሰሉ ብዙ የሴራ ስብጥሮች ሲሆኑ፤ በዋነኛነት ግን ወያኔ ፣ ሻቢያ፣ ኦነግና አንጃዎቹ ናቸው።

ዳያስፖራው ኢትዮጵያን በዩጐዝላቪያ፣ በሶማሊያና በርዋንዳ መነፅር እየተመለከተና አስጊ ሁኔታዎችን እየሳለ ጠላቶቿ ወያኔ፣ ሻቢያና ኦነግ የፈጠሩትን የመፍረስንና የመበታተንን ፕሮፖጋንዳ አሜን ብሎ ተቀብሏል። ይህ ደግሞ በተራው ጭልጥ ወዳለ ኦነግንና አንጃዎቹን ማባበልና ካላንዳች ቅድመ-ሁኔታ አብሮ ወደ መደራጀቱና ወያኔ- ሻቢያ-ኦነግ ጠቀም ወደሆነ ስህተተኛና ውግዝ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ከትቶቷል።

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የፖለቲካ ዓላማና ቁርጠኛ አቋም ኦነግንና አንጃዎቹን፣በዳያስፖራ የተሰበሰቡ ጠላቶቹንና ስብጥር ሴራዎችን ሁሉ ከወያኔና ከሥርዓቱ ጋር አብሮ መደምሰስና ኢትዮጵያን፣ ሕዝቧንና እምነቷን ወደ ቀድሞ መሰረታቸው መግጠምና በአስተማማኝ ማረጋገጥ ነው። ስለሆነም ከዚህ ውጭ ኢትዮጵያ መፍትሄ የማትጠብቅ መሆኑ በጥብቅ እንዲታወቅ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በግልጥና በይፋ በዚህ መግለጫ ያስጠነቅቃል።

ከ7ሺህ ዓመታት በላይ አገርና መንግሥት ሆና ፀንታ የኖረች ኢትዮጵያ ፣ እንደ ዮጐዝላቪያ፣ ሶማሊያና ርዋንዳ ጨቅላ አገር አይደለችም። ወያኔ ፣ ኦነግና ሻቢያ ደግሞ ፣ ኢትዮጵያን የማፍረስ አህዙም- ዘዴውም የሌላቸው እንጭጭ አናሳን የሆኑና በአንድ ሙብረቃዊ አፐሬሽን የሚደመሰሱ ናቸው።

ስለዚህ ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነትና ለአረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማ የቆምህ ሁሉ፤ በጠላቶችህ ፕሮፓጋንዳና በዳያስፖራ አፍራሽ ደማጐጂና ጫጫታ ፈጽሞ አትስጋ- አትሸበር ! ! !
አገርህ ካለትናንት ቀዳማዊ፣ ካለዛሬ ማዕከላዊ፣ ካለነገ ዘላለማዊ ስለሆነች፤ ከማይገሰሰው አገራዊ ሕልውናዋና ከገናና ታሪኳ ጋር ታፍራና ተከብራ ፣ በልጽጋና አይላ ትኖራለች።

## እምቢ ለአገራችን ! !

## እምቢ ለኢትዮጵያችን ! !

## ሞት ለጠላቶቻችን ! ! ! ! !